6ኛ ዓመት ቁጥር 5
6th Year No. 5

ሐረር ሐምሌ 18 ቀን 1993
HARAR JULY 25/2001

የሐረሪ ሕዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE

| | | |
|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ ብር 0.50 | በሐረሪ ሕዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272 |

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 26/1993 ዓም
የሐረሪ ህዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የዉሃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 15/1991 እና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 22/1992ን በድጋሚ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 26/1993.......... ገጽ 238
የዉሀና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን የውሀ ታሪፍ ማሻሻያ የክልሉ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ደንብ ቁጥር 4/1993 ዓ.ም. . . ገጽ 242/3

## አዋጅ ቁጥር 26/1993 ዓም
## የሐረሪ ህዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የዉሃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር15/1991 እና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 22/1992ን በድጋሚ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የሐረሪ ህዝብ ክልል የዉሃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 15/1991 እና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 22/1992ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በሐረሪ ህዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ሕገ-መንግስት አንቀፅ 26 ንዑስ አንቀፅ 2/ሀ/ መሰረት የሚከተለዉ ታዉጇል።

1 አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የሐረሪ ህዝብ ክልል የዉሃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 15/1991 እና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 22/1992ን በድጋሚ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 26/1993 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2 ማሻሻያ

ክልሉ ዉኃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 15/1991 እና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 22/992 እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል።

1. የማሻሻያ አዋጅ አንቀፅ 9 ተሰርዞ በሚከተለዉ አዲስ አንቀፅ 9 ተተክቷል።

"9. የቦርዱ አደረጃጀት

የሐረሪ ህዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የዉሃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 15/1991 እና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 22/1992ን በድጋሚ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 26/1993. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .ገጽ 239

1· ቦርዱ በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይቋቋማል፣ ባለሥልጣኑም በዚሁ የሥራ አመራር ቦርድ ይመራል።
2· የቦርዱ ተጠሪነት ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይሆናል።
3· የቦርዱ አባላት የሥራ ዘመን በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴዉ ይወሰናል።
4· የቦርዱ ሰብሳቢና አባላት አበል በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይወሰናል።
5· የቦርዱ አባላት ስብጥር ከሚከተሉት አካላት ይሆናሉ።

ሀ/ የክልሉ ፕሬዝዳንት............ሰብሳቢ
ለ/ የኢኮኖሚ ዘርፍ ሐላፊ.....አባል
ሐ/የዉ/ማ/ኢ/ቢሮ ኃላፊ.........አባል
መ/የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት ሹም.......................................አባል
ሠ/በሀረር ከተማ የሚገኙ ጤና ተቋማት የሚወከል ባለሞያ.......................................አባል
ረ/ከሐረር ከተማ ነዋሪ ህዝብ የሚወከል ሁለት ተወካዮች..............................አባላት
ሰ/ የሐረር ከተማ ንግድ ህብረተሰብ ተወካይ.......................................አባል
ሸ/ከባለሥልጣኑ ሰራተኞች የሞያ መህበር .......................................አባል
ቀ/የባለሥልጣኑ ሥራ አስኪያጅ ድምፅ የሌለዉ የቦርዱ ፀሐፊ ይሆናል።"

2. በማቋቋሚያ አዋጁ አንቀፅ 11 ስር የሚከተለዉ አዲስ ንዑስ አንቀፅ /3/ እና /4/ ተጨምሯል።

"3. የተዘረጉ የዉሃ መስመሮች በሊዝ በያዘዉ ወይም በሚጠቀሙበት ንብረት ላይ ማለፉን እንዲያዉቅ የተደረገ የሊዝ ያዥ ወይም ሌላ ህጋዊ ተቃዋሚ እንደንብረቱ ባለቤት ሆኖ የተዘረጉ መስመሮችን የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት።"

"4 ማንኛዉም ባለንብረት፣ ባለይዞታ ወይም በሊዝ ያዥ ባለስልጣኑ መስመርቶችን ለመዘርጋት ለመጠቀም፣ ለመቆጣጠር፣ ለመንከባከብ ወይም ለመጠገን የሚካሄደዉን ሥራ ማደናቀፍ የለበትም ወይም አይችልም።"

3. የማቋቋሚያ አዋጁ አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 2 ተሰርዞ በሚከተሊዉ አዲስ ንዑስ አንቀፅ ተተክቷል።

"2. ባለስልጣኑ በአገልግሎት ክልሉ ዉስጥ የዉሃ እና ፍሳሽ ሥራዎችን የሚገነባዉ ወይም የሚዘረጋዉ የከተማን መሪ ፕላን በመከተል ይሆናል።"

4. በማቋቋሚያ አዋጅ አንቀፅ 16 ሥር የሚከተለዉ አዲስ ንዑስ አንቀፅ 6 እና 7 ተጨምሮበታል።

"6. ለከተማዉ ህብረተሰብ ዉሃ አቅርቦት የሚረዱ በሥሩ የሚገኙትን ነባር የዉሃ መገኛ ምፍራዎችን እና መሥመሮችን ለመጠገን፣ የማሻሻል እንዲሁም አዳዲስ የዉሃ ተቋማት የማጥናትና የመገንባት።

7. በአገልግሎት ክልሉ የፍሳሽ መሥመሮችን የመዘርጋት፣ የማደስ፣ የመጠገን ፣ የማሻሻል እንዲሁም ወደ ፍሳሽ መስመሩ የሚገባዉን የፍሻሽ አይነት መጠን የመወሰን፣ ከዚሁ ጋር የተያያዙ የጤናማነት ደረጃዎችንና መመዘኛዎችን የመጠበቅና የመተግበር"

5. የማቋቋሚያ አዋጁ አንቀፅ 19 ተሰርዞ በሚከተለዉ አዲስ አንቀፅ 19 ተተክቷል፡፡

"19. <u>የቦርዱ ስብሰባ</u>

1. ቦርዱ መደበኛ የሆነ ወርሃዊ ስብሳባ ይኖረዉል ሆኖም እንደአስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡
2. ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ስብሰባዉ ላይ ከተገኙ ምዕላተ ጉባዔ ይሆናል፡፡
3. ቦርዱ ዉሳኔ የሚያሳልፈዉ በስብሰባዉ በተገኘ አባላት ድምፅ ብልጫ ይሆናል ሆኖም ድምፅ እኩል ለእኩል ከሆነ ወይም የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢዉ ወደ አለበት ወገን ያለዉ ሃሳብ የቦርዱ ዉሳኔ ሆኖ ያልፋል፡፡
4. የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነዉ ቦርዱ ዝርዝር የስብሰባዉ ሥነ-ስርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡"

6. በማቋቋሚያ አዋጁ አንቀፅ 20 ስር የሚከተለዉ አዲስ ንዑስ አንቀፅ /12/ /13/ እና /14/ ተጨምሯል፡፡

"12. ቦርዱ የባለሥልጣኑን የሥራ እንቅስቃሴ በበላይነት ይመራል ይከታተላል፡፡

13. የባለሥልጣኑን መዋቅርና ደሞዝ እንደአስፈላጊነቱ አስጠንቶ ያፀድቃል፡፡

14. የባለሥልጣኑን የአገልግሎት ታሪፍ እንደአስፈላጊነቱ በየጊዜዉ አስጠንቶ በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያፀድቃል፡፡"

7. የማቋቋሚያ አዋጁ አንቀፅ 22 ተሰርዞ በሚከተለዉ አዲስ አንቀፅ 22 ተተክተዋል፡፡

"22. <u>የሥራ አስኪያጁ ሥልጣን፣ ተግባርና ኃላፊነት፡-</u>

1. የባለሥልጣኑ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለቦርዱ ሆኖ የባለሥልጣኑን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴና አስተዳደር ለማከናወን ኃላፊና ተጠሪ ይሆናል፡፡

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ አንድ ላይ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የባለሥልጣኑ ሥራ አስኪያጅ የሚከተሉትን ዝርዝር ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

ሀ/ በማቋቋሚያ አዋጁ አንቀፅ 16 እና በዚህ አዋጅ አንቀፅ 5 ሥር የተመለከቱትን የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ እንዲዉሉ ያደርጋል፡፡

ለ/ የባለሥልጣኑን የሥራ እንቅስቃሴ ያቅዳል፣ ያደራጃል፣ ያስተዳድራል ይመራል ይቆጣጠራል፡፡

ሐ/ ከሦስተኛ ወገን ጋር በሚደረገዉ ግንኙነት እንዲሁም ባለሥልጣኑ በሚከሰስበትም ሆነ በሚከስበት ወቅት ባለሥልጣኑን ይወክላል፡፡

መ/ በቦርዱ ተመስደቅ እንደተጠበቀ ሆኖ የባለሥልጣኑን የሥራ ኃላፊዎች በባለሥልጣኑ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የመቅጠር፣ የመመደብ የሥራ ዝርዝራቸዉን የማዉጣት፣ የዲሲፕሊን እርምጃ የመዉሰድ፣

የሐረሪ ህዝብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የዉሃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 15/1991 እና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 22/1992ን በድጋሚ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 26/1993. .................................... .ገጽ 241

ከሥራ የማሰናበት... ወ.ዘ.ተ. ያከናዉናል።

ሠ/ በአዋጅ ቁጥር 42/1985 መሰረትና በቦርዱ በሚወጡት መተዳደሪያ ደንቦች መሰረት ሌሎች የባለሥልጣኑን ሰራተኞች የመቅጠር የመመደብ የማሳደግ የሥራ ዝርዝራቸዉን የመግለፅ ፣ እርምጃ የመዉሰድ ከሥራ የማሰናበትና ሌሎች አስተዳደራዊ ተግባሮችን ያከናዉናል።

ረ/ የባለሥልጣኑን ዓመታዊ የሥራ እቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ በቅማረብ ሲፈቀድ በሥራ ላይ ያዉላል ይቆጣጠራል።

ሰ/ የባለሥልጣኑን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ በተመለከተ ለቦርዱ ሪፖርት ያቀርባል።

ሸ/ የባለሥልጣኑን ሂሳብ ያንቀሳቅሳል በአግባቡ እንዲያዝም ይቆጣጠራል።

ቀ/ ለባለሥልጣኑ ሥራ አፈፃፀም ቀልጣፋ የሆኑ የዉስጥ ደንቦች መመሪያዎችንና የሥራ ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል በቦርዱ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያዉላል አፈፃጸማቸዉን ይቆጣጠራል።"

8. የማቋቋሚያ አዋጁ አንቀፅ 7፣ 8፣ 9፣ 10፣ 11፣ 12፣ 13፣ 14፣ 15፣ 16፣ 17፣ 18፣ 19፣ 20፣ 21፣ 22፣ 23፣ 25፣ 26፣ 27፣ 28፣ 29፣ 30፣ 31፣ 32፣ 33 እና 34 እንደቅደም ተከተላቸዉ አንቀፅ 6፣ 7፣ 8፣ 9፣ 10፣ 11፣ 12፣ 13፣ 14፣ 15፣ 16፣ 17፣ 18፣ 19፣ 20፣ 21፣ 22፣ 23፣ 24፣ 25፣ 26፣ 27፣ 28፣ 29፣ 30፣ 31፣ 32፣ 33 እና 34 ሆነዋል።

3 አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በሐረሪ ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሐምሌ 18 ቀን 1993 ዓ.ም
ሐረር
ፋአድ ኢብራሂም
የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
ፕሬዝዳንት

---

## የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ
## ደንብ ቁጥር 4/1993
## የዉሀና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን የዉሀ የታሪፍ ማሻሻያ
## የክልሉ ስራ አስፈጻሚ ደንብ ቁጥር 4/1993

በሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሕገ መንግስት አንቀጽ 33 ንዑስ አንቀጽ 10 እና በክልሉ የዉሀና ፍሳሽ አገልልሎት ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 15 /1991 አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ይህን ደንብ አዉጥቷል ።

1. አጭር ርእስ

ይህ ደንብ "የውሀና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን የውሀ ታሪፍ ማሻሻያ የክልሉ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ደንብ ቁጥር 4/1993" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2. ማሻሻያ

የሐረር ከተማ የዉሃ አቅርቦት ታሪፍን በመቀየር የሐረር ከተማ ዉሃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለሥልጣን ደረጃ በደረጃ አገልግሎት የመስጠት አቅሙን አዳብሮ ከድጎማ ለማላቀቅ የሚረዳ በትሮፒክስ ኮንሰልቲንግ ኢንጅነርስ አማይነት ጥናቱን ቀርቦ ህብረተሰቡ እንዲያቀዉ ተደርጓል። በዚህ መሠረት

### OPTION 1 FULL COST RECOVERY

| | | |
|---|---|---|
| Public tab | | Birr 1.15 |
| $1^{st}$ band | $0\text{-}5m^3$ | Birr 2.25 |
| $2^{nd}$ band | $6\text{-}10m^3$ | Birr 4.05 |
| $3^{rd}$ band | $11\text{-}30m^3$ | Birr 6.08 |
| $4^{th}$ band | $>30m^3$ | Birr 12.69 |

### OPTION 2 DEPRECLATION & OPERATION & MAINTENANCE COST RECOVERY

| | | |
|---|---|---|
| Public tab | | Birr 1.15 |
| $1^{st}$ band | $0\text{-}5m^3$ | Birr 2.15 |
| $2^{nd}$ band | $6\text{-}10m^3$ | Birr 2.25 |
| $3^{rd}$ band | $11\text{-}30m^3$ | Birr 4.05 |
| $4^{th}$ band | $>30m^3$ | Birr 2.50 |

### OPTION 3 OPERATION & MAINTENANCE COST RECOERY

| | | |
|---|---|---|
| Public tab | | Birr 1.00 |
| $1^{st}$ band | $0\text{-}5m^3$ | Birr 1.25 |
| $2^{nd}$ band | $6\text{-}10m^3$ | Birr 1.60 |
| $3^{rd}$ band | $11\text{-}30m^3$ | Birr 2.00 |
| $4^{th}$ band | $>30m^3$ | Birr 2.50 |

የሚሉ አማራጮች ቀርበዉ ከህብረተሰቡ የመክፈል አቅሙ እና የመ/ቤቱ ደረጃ በደረጃ በገቢዉ እንዲተዳደር ማድረግ ይቻል ዘንድ በሶስተኛ አማራጭነት የቀረበዉ ታሪፍ ማለትም፡-

**OPTION 3 OPERATION & MAINTENANCE COST RECOERY**

| | | |
|---|---|---|
| Public tab | | Birr 1.00 |
| 1st band | 0-5m$^3$ | Birr 1.25 |
| 2nd band | 6-10m$^3$ | Birr 1.60 |
| 3rd band | 11-30m$^3$ | Birr 2.00 |
| 4th band | >30m$^3$ | Birr 2.50 |

ተቀባይነት አግኝቶ በክልሉ ም/ቤት ፀድቋል።

## 3. የተሻሩ ደንቦችና መመሪያዎች

ይህንን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ ፣ መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ ደንብ ውስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም ።

## 4. ቅጣት

በዚህ ደንብ የተወሰነውን የተላለፈ ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት በወንጀለኛ መቅጫ ህግ መሰረት ይቀጣል ።

## 5. ደንቡ የሚጸናበት ግዜ

ይህ ደንብ በሐረሪ ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ግዜ ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

ሐረር ሐምሌ 18 ቀን 1993 ዓ.ም

ፉአድ ኢብራሒም

የሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ፕሬዝዳንት